BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## Routine: What time do you get up?

## ከእንቅልፍህ የ ምትነ ሳውስንት ሰዓት ላይ ነ ው?

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዚህ ክፍል መቼ ከአልጋ እንደሚነሱ 'get up' እና መቼ እንቅልፍ እንደሚተኙ 'go to bed' መናገርን ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች መቼ ከእንቅልፍ ነቅተው ከአልጋ ላይ እንደሚነሱ ሲያወሩ ያዳምጡ።

***Sian***
*Hi Phil, when do you get up?*

***Phil***
*I get up at six o'clock.*

***Sian***
*What time do you go to bed?*

***Phil***
*I go to bed at ten o'clock.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
በመጀመሪያ ሻን ፊልን መቼ እንደሚነሳ 'gets up' ጠየቀችው።

*When do you get up?*

**ዘሩባቤል**
ፊል 'six o'clock' አስራ ሁለት ሰዓት ላይ እንደሚነሳ ተናገረ። ሰዓቱን ለመግለፅ ቁጥሩን ከተናገርን በኋላ 'o'clock' እንጠቀማለን። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*I get up at six o'clock.*

**ዘሩባቤል**
ከዚያም ሻን መቼ እንደሚተኛ 'go to bed' ጠየቀችው። ስለጊዜ ለመጠየቅ 'when' ወይንም 'what time' መጠቀም እንችላለን። በሁለቱ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*What time do you go to bed?*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
ፊል 'ten o'clock' አራት ሰዓት ላይ እንደሚተኛ ነገራት። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I go to bed at ten o'clock.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፥ አሁን የተለያዩ ሰዎች መቼ እንደሚተኙ እና መቼ እንደሚነሱ ሲነጋገሩ በማዳመጥ እርስዎ ካሉት ጋር ያመሳክሩ።
ጆሴፍ የሚነሳው አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ሲሆን የሚተኛው ደግሞ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ላይ ነው።

*Hi Joseph, what time do you get up?*

*I get up at six o'clock.*

*What time do you go to bed?*

*I go to bed at one o'clock.*

**ዘሩባቤል**
እሺ፤ አሁን የቅድሙን ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛውን አረፍተ ነገር ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።
እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጧቸዋል።

*When do you get up?*
*When do you get up?*

*I get up at six o'clock.*
*I get up at six o'clock.*

*What time do you go to bed?*
*What time do you go to bed?*

*I go to bed at ten o'clock.*
*I go to bed at ten o'clock.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*መቼ ነው የሚነሱት?*
*When do you get up?*

*አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ነው የምነሳው።*
*I get up at six o'clock.*

*ስንት ሰዓት ላይ ነው የምትተኛው?*
*What time do you go to bed?*


© British Broadcasting Corporation 2018

*አራት ሰዓት ላይ ነው የምተኛው።*
*I go to bed at ten o'clock.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ግሩም፥ አሁን ስለሚተኙበት እና ስለሚነሱበት ሰዓት መጠየቅ እና መናገርን አውቀዋል። ለሻን ምላሽ በመስጠት እና እነዚህ ነገሮች ሰዎች ስንት ሰዓት ላይ እንደሚያከናውኑ በመጠየቅ ልምምድ ያድርጉ።

*When do you get up?*
*What time do you go to bed?*

**ዘሩባቤል**
አሁን ሙሉውን ንግግር ያዳምጡና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Sian***
*Hi Phil, when do you get up?*

***Phil***
*I get up at six o'clock.*

***Sian***
*What time do you go to bed?*

***Phil***
*I go to bed at ten o'clock.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሰዎች ስንት ሰዓት ላይ እንደሚተኙ እና እንደሚነሱ በእንግሊዝኛ መጠየቅን ችለዋል። ጓደኛ ይፈልጉና ስንት ሰዓት ላይ እንደሚተኙ እና እንደሚነሱ በእንግሊዝኛ በመጠየቅ ይለማመዱ። ለተጨማሪ ጠቃሚ የእንግሊዝኛ ንግግሮች በሚቀጥለው መሰናዶ ይጠብቁን።


© British Broadcasting Corporation 2018